Amharic Translation

## የ2018 የዓለም ቴአትር ቀን የአፍሪካ መልዕክት

## ዌሬ ዌሬ ሊኪንግ ኚፖ ከአይቮሪኮስት

## ሁለገብ ከያኒ

ከቀኖች ባንዱ ቀን

ሰው ከመስታወት(ከተመልካች) ፊት ቆሞ

በራሱ ጥያቄ ራሱ ተገርሞ

ራሱን ማፋጠጥ፣ ራሱን መፈተሽ ፈልጓል

እዛው መስታወቱ(ተመልካች) ፊት ቆሟል፡፡

ራሱን ለማግኘት ራሱ ጠይቆ ራሱ ለመመለስ

ራሱን ለመካብ ብሎም ራሱን ለመውቀስ

ደግሞም ለመሳቅ ሲያሻውም ለማልቀስ፡፡

በራሱ ጥያቄ ደግሞም በምላሹ በራሱ ለማላገጥ

በብልጠቱ ለመንከትከት በሞኝነቱ ለማግጠጥ፡፡

መስታወቱን "ጤና ይስጥልኝ" ሊለው

ሊመርቀው ሽቶ

ራሱን ስላሳየው ይህን ቅጽበት ሰጥቶ

የከይሲ ፍላጎት ጭንቀት፤

ለጥቆም የእፎይታ ቅጽበት!!!

ሰላም ይለዋል ጭንቅላቱን ይነቀንቃል

አክብሮቱን መግለጫ ምስጋና ቢሆነው ቃል፡፡

በጥልቀት ሰላሙን እየፈለገ ነበር

ከራሱ ለመታረቅ ከመስታወቱም ለመፋቀር፡፡

በዛን ቀን ቴአትር እየሰራ ነበር……

የህይወት ውድቀቱን ጉራማይሌ ማንነቱን

ንቆ ተጠይፎ  ዝብርቅርቅ ስሜቱን

ራሱን ያስፈራራል የሰው ድርጊት እየቀዳ

መላ ቅጧን ካጣች አለም መገፋትን እያስረዳ፡፡

የገዛ ጥላቻውን ሰብዓዊነቱን ያጠፋውን

የገዛ ተንኮሉን መቅሰፍትን ያስፋፋውን

ራሱን እያናገረው ነበር….

በዓለት ስሜቱ ራሱን ያደንቃል

ታላቅነትን ይመኛል በውበት ይስቃል፡፡

የተሻለ ሰውን የተሻለች አለም

በምናቡ ሰርቶ በሃሳቡ ሲተለም

በእጆቹ ታታሪነት

በአእምሮው  ስክነት!!!

በመስታወቱ ውስጥ የቆመው ምግባሩ

ከራሱ ለራሱ ቢሆን ንግግሩ

ከመስታወቱም ጋር ፍላጎት ቢጋሩ

ምኞቱ ነበር…ውጥን ባይሰበር!

ዳሩ ያውቀዋል ወክሎ እንደቆመ

የሌላውን ህመም እሱ እየታመመ

ጅልነትን ለብሶ ሌላውን ለመምሰል

ህሊናዊ ክውን የስሜት መብሰልሰል

ድጋሚ ለመፍጠር አለምን ለማብሰል፡፡

ቴአትር እየሰራ ነበር….

ተስፋውን ተነጥቆ እንደሞተ ዘመድ

ተክዞ ቢቀርም ብቻውን ከመንገድ

በመርማሪ ቃላት በሚሞግት ፊቱ

እንደሚሆን ያምናል ሁሉም እንደጥንቱ፡፡

በዚች ነጠላ ምሽት አለም እንደምትቀየር

በቴአትር ጥበብ እንደምትዘየር!

በቀውስ ዓይኖቹ በጣፋጭ ቃሎቹ

በደላይ ፈገግታው በጨዋታ ለዛው

ወይ በሚሞሉ አልያም በሚያጎድሉ

በገዛ ቃላቱ በቋንቋ ስባቱ

ቀዶ ይጠግናል ተዓምር ፍለጋ

አዎ! ቴአትር ላይ ነበር ለጥበብ ሲተጋ!!!

እንዲህ ነው

በቤታችን በአፍሪካ በሰብዓዊነት ዋርካ

በተለይ ከተገኘሁበት ካደግኩበት ሀገር

ስቄ ከኖርኩበት ከካሚቴ[1] መንደር፤

ከቶ አንጨነቅም፤መከፋት አናውቅም፡፡

ሁሌም እንስቃለን አዎ እንስቃለን

በለቅሷችን እንኳ ፈገግታ እናውቃለን፡፡

መሬቱ ቢያናደን ቢሆንብን ሙጫ

መቼም አንመለስ ለማለት በእርግጫ፡፡

በቢኮውትሲ[2] ወይም በግቤግቤ[3] ሰብነት ይሰፋል

የአስፈሪነት ጭምብል ተበጣጥሶ ይጠፋል፡፡

ግላ'ን[4] እንለብስና በዋበሊ[5] ጅብፊት

በፓኒኢጎ[6] ሃይል እንቆማለን ከፊት፡፡

ማያገናዝቡ! እብሪተኛ ደንቦች ይመረመራሉ

አስፈሪ ጭምብሎች ሐቅን ይገልጣሉ፡፡

አሻንጉሊቶቹ ደሞ ይወዱናል

ፈጣሪያቸውን እጅግ ያከብሩናል፡፡

በሙዚቃዊ ምት በስልት የተሞሉ

በአፋዊ ቃል ስርዓት ያበጃሉ

ያስጨነቋቸውን መሬት ይጥላሉ!!!

እየተወዛወዙ እያወዛወዙ በሚቀሰቅሱ

የተኛን ከእንቅልፉ ቶሎ በሚያስነሱ

በድግምት አዙሪት ወረው ሊቀደሱ!!!

የሰብዓዊነት ጸጋ የተሸለምነው ፈገግታ

ዘወትር ያሳየኛል የመኖርን ደስታ፡፡

የዘመናት ባርነት ጨቋኝ ቅኝ አገዛዝ

ሰውን ያህል ፍጡር እንደ እቃ ማጋዝ

ሀብታችንን ዘርፎ ጥይት ቢያስጨንቀን

ከቶም ሳቃችንን አልቻለም ሊነጥቀን፡፡

ጨቅላን የዘረፈ ከእናቱ እቅፍ

መድሎ ዘረኝነት የማይነገረው ግፍ

[1] ካሚቴ፡- የካሚቴ ነዋሪ ወይም 'የጥቁሮች ምድር' ስንጠቀልለው ደግሞ አፍሪካ ማለትም ነው፡፡ ካሚቴ የአካባቢውን ተወላጆችን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ያሉ የካሚቴ ዘር ግንድ ያላቸው በመላው ዓለም የተበታተኑ ዲያስፖራዎችን ጨምሮ የአካባቢውን እምነት የሚከተሉ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ጭምር ያካትታል፡፡

[2]ቢኮውትሲ ሀ.ኮውት፡ ምት ለ. ሲ፡መሬት፡፡ በደቡብ ካሜሮን የሚገኙት የፋንቤቲዎች ውዝዋዜ ሲሆን ሴቶች መሬቱን በኃይል እና በፍጥነት በመርገጥ ከእናት ምድር በረከትን የሚለምኑበት የውዝዋዜ ስልት ነው፡፡ በአለምአቀፍ ደረጃ ታዋቂ ለሆኑበት ስመጥር አርቲስቶች ምስጋና ይግባና ዛሬ በሀገሪቷ ወጣቶች በብዛት የሚዘወተር የውዝዋዜ አይነት ሆኗል፡፡

[3]ግቤግቤ በአይቮሪኮስት የሚገኘው የቤቴስ ማህበረሰብ እንደ ለቅሶ እና ፌሽታ ለሚጠይቁ ህዝባዊ ስነ-ስርዓቶች የሚጠቀምበት ባህላዊ ውዝዋዜ ነው፡፡ .

[4]ግላ' በምእራብ አፍሪካ የሚገኙ የዌ እና ዎቤ ህዝቦች የእምነት ስርዓት ነው፡፡ አስፈሪ ገጽታ ያላቸው ጭምብሎች የማህበረሰቡ አኗኗር እና እምነት መሰረት ናቸው፡፡
[5]ዋበሊ በሰሜን አይቮሪኮስት በሴኑፎ ማህበረሰብ ወስጥ የሚገኝ፤ እሳት የሚበላ ተዋናይ፣ የጅብ ጭምብል ለብሶ የሚያደርገው ክዋኔ ነው፡፡ ዋበሊ እውቀት እና ኃይልን ይወክላል፡፡
[6]ፖኒኢጎ በሴኑፎዎች ኃይማኖታዊ ስርዓት ውስጥ ሌላኛው የጭምብል ክዋኔ ሲሆን በተቀደሰ ጫካ ውስጥ ይከወናል፡፡

የአባትነት ክብራችንን ትዕግስትን የታደለ

ሰብዓዊ ፍቅርን በእናት ስስት ያበቀለ

ሊወስደው አልቻለም ፈገግታችን አለ፡፡

አለም ላይ እንዳለው ልብን የሚነካ

ጥላቻን አውግዞ ሰላም የሚተካ

ቴአትር ከዋኝ ነን ሁሌም በአፍሪካ!!!

የአለምአቀፉ ቴአትር ተቋም በዚህ ዓመት በልዩ ስ-ነስርዓት በሚያከብረው የቴአትር ቀን እና የተቋሙ ሰባኛ አመት ክብረ-በዓል አህጉራችንን ወክዬ የእናት አፍሪካን የሰላም መልዕክት ለማስተላለፍ በመቻሌ ልዩ ክብር ይሰማኛል፡፡ ሰላማዊ የቴአትር መልዕክት ማለቴ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አህጉራችን ሰላም ያጣች ምድር ተደርጋ ስለምትቆጠር ነው፡፡ ነገር ግን በመላው አለም የሚፈጸመው መጥፎ ተግባር ሁሉ በጥቂቶች እንጂ በብዙሃን ፍላጎት አይደለም፡፡ በወላጆቻቸው ክንድ ላይ ያሉ ህጻናት እንኳ የሰላምን ተስፋ ይመኙ የለም እንዴ? እውነታው ይሔ አይደለም እንዴ?

ከምንጊዜውም በላይ የቴአትራችን መሪ ቃል ሰብዓዊነት መሆን አለበት፡፡ገገር ሃሳቡ የሰው ልጅ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተለይም የውስጥ ሃሳባቸውን ለዓለም ማጋራት ለሚፈልጉ ቴአትር በሯን መክፈት አለባት፡፡ ለራሳቸውም ሆነ እርስ በርሳቸው የተሻለ ክብር እንዲኖራቸው ለማድረግ! ለምርጥ ሰብዓዊ እሴቶች በማዳላት! የተሻለ ሰብዓዊነት በምድር ላይ ለሰው ልጅ ሁሉ እንደሚሰፍን ተስፋ በማድረግ! እውቀት እና መግባባትን ማምጣት የቴአትር ችሎታ ነውና፡፡ የሰው ልጆችን ባህል ተጠቅሞ ሰው ሰራሽ ድንበሮችን በፍቅር የሚያፈርስ ቴአትር ብቻ ነው፡፡ የሁሉንም ቋንቋ የሚናገር እጅግ ትሁት፣ የሁሉንም ስልጣኔ የሚያነሳ ዘመናይ፣ ሰዋዊ ሃሳብን የሚያንጸባርቅ፣ በነፍስ ሰንሰለት የተሳሰረ አንድነትን የሚገልጽ ድንቅ ጥበብ ነው፤ ቴአትር!!
ህልውናውን የሚጋፉ ኃይላት ቢኖሩም ቴአትር ግን ግድም አይሰጠው፡፡በጥልቅ እርስ በርስ እንድንተዋወቅ ይፈልጋል እንጂ! በልባዊ ፍቅር መንፈስን በሚያድስ ሰላም ራሳችንን (ሰውነታችንን) እንድንወደው ያደርጋል እንጂ፡፡

ውክልና ወደ ተሳትፎ ሲቀየር መፈጸም ያለብንን የውዴታ ተግባር ያስታውሰናል፤ የቴአትር ኃይል አብረን እንድንስቅ አብረን እንድናለቅስ ያደርገናል፡፡

ቸልተኝነታቸውን በማጥፋት  እውቀታቸውን በማብዛት ሰው እንደ ጥንቱ የሰው ትልቁ ሀብቱ ይሆናል፡፡ ቴአትራችን እነዚህን ሁሉ ሰብዓዊ እሴቶች እና ሰናይ ምግባሮች በድጋሚ መፈተሽ ይፈልጋል፡፡ እነዚህን ሁሉ የሰላም ውጥኖች፤ በህዝቦች መካከል የነበረ ወንድማማችነትን ዳግም

ማስረጽ ይሻል፡፡ አለምአቀፉ የትምህርት፣ የሳይንስና እና የባህል ተቋም እንደሚያበረታታው

በቅድሚያ እኛ ቴአትረኞች እነዚህን አንገብጋቢ እና ፋታ የማይሰጡ ጉዳዮችን መንፈሳችንን ሰብስበን፣ ከራሳችን ጋር መክረን፣ በጥልቀት ዘክረን ለተመልካቾቻችን ማጋራት አለብን፡፡

ለዚህም ነው በቅርቡ የሰራነው "ለርብህ ዲዩ" ቴአትራችን ላይ መሪ ገጸ-ባህሪያችንን የኪንዳክን[7] ምክር አጽንኦት ሰጥቶ እንዲህ እንዲናገር ያደረግነው፡

" እግዚአብሔር እንደ ትልቅ ዛፍ ነው

በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ብቻ የሚመለከት

ከመንበሩ ሆኖ ላመኑት የሚከሰት፡፡

ማንም

በዛፉ አናት ላይ በክንፎቹ ቢበር

አበባ ነው የሚያገኝ የፍራፍሬ ዘር፡፡

ማንም

ከዛፉ ስር 'ሚኖር፤ ስለስሩ ታሪክ፤ የበለጠ ያውቃል

ራሱን ቅርንጫፍ አድርጎ፤ ዛፉንም ያደንቃል፡፡

እነሱ ህግ ያላፋለሱ

የህይወት ጥያቄ ይዘው የተነሱ

ሌሎች ማይችሉትን እነሱ ያያሉ

የተመረጡቱ ሚስጥር ይገልጣሉ፡፡

የቅርፊቱን ድርቀት ልጠው ይጥላሉ

የፍሬውን ሀሴት ጣዕም ያገኛሉ፡፡

ግና
አሁንም አሁንም በሳይንስ ፈጠራ

በስጋዊ ዓይን በጭንቀላት ስራ

ዛፉን ለመመርመር ምንም ቢዳክሩ

ከህዋ ላይ ወጥተው ሀገርን ቢመሩ

አልያም

በጎዶሎ እውቀት ከፍታን ቢመኙ

በአስተዋይ አእምሮ ምድርን ቢጎበኙ

ማንም አይቻለው ባህሩን ለማለፍ

ከተሰጠው በላይ ሁሉንም ለመጭለፍ፡፡

ሁሉን አታገኝም ምን ብትፍጨረጨር

መለኮታዊውን ዛፍ ካልሆንከው በስተቀር፡፡

እናስ እኛ የቱ ጋር ነን?

አሁንም ሰዎች ነን?"

በመሆኑም በመላው ዓለም ያሉ ቴአትሮች ሁሉ የዓለም ቴአትር ተቋም ሁለንተናዊ አላማን ለማሳካት በመቻቻል እና እርስ በርስ በመፈቃቀድ በጋራ ይሰራሉ፡፡ የተቋማችንን ሰባኛ አመትን ስናከብርም በጠንካራ ቴአትራዊ ክንውን፣ ሰላምን በአለም ዙሪያ እንደምናሰፍን እናምናለን፡፡

## የዌሬ ዌሬ ሊኪን ኚፖ አጭር ግለ-ታሪክ

ዌሬ ዌሬ ሊኪን ኚፖ የተወለደችው እንደ አውሮፓዉያኑ አቆጣጠር በሜይ አንድ በ1950 ካሜሮን ውስጥ ቦንዞ በተባለ ስፍራ ነው፡፡ ከ18 ዓመቷ ጀምሮ አይቮሪኮስት ውስጥ የኖረችው ዌሬ ዘርፈ-ብዙ የኪነ-ጥበብ ሰው ነች፡፡ እንደ ጸሐፊ ልብወለዶችን፣ ተውኔቶችን፣ ወጎችን፣ የግጥም መድብሎችን፣ የስዕል መጽሃፎችን ጨምሮ ወደ ሰላሳ የሚጠጉ የህትመት ውጤቶችን ለአንባብያን አድርሳለች፡፡ በ1968 ዓ.ም እጇ የስዕል ብሩሽ ካነሳበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ዓውደ-ርዕዮችን በመላው ዓለም ለማቅረብ ችላለች፡፡ ታላቅ ተልዕኮን ያነገበች ጸሐፊ-ተውኔት ከመሆኗም ባሻገር ቴአትሮቿን የአፍሪካ ኦፔራ ካሰኙላት አብይ ነጥቦች መካከል ለቴአትር በምትሰላቸው ግዙፍ ዳራዊ ቅቦችም ትታወቃለች፡፡ ዌሬ የመድረክ እና የፊልም ተዋናይ እንዲሁም የራፕ ሙዚቀኛም ነች፡፡

ከ1979-1985 *በአቢጃን ዩኒቨርሲቲ የትራዲሽናል ፔዳጎጂካል ቴክኒክስ* ተመራማሪ ሆና ባገለገለችበት ወቅት ለትውፊታዊ ቴአትር ዳግም ንቅናቄ ትልቁን ሚና የተጫወተች ሲሆን *ካይአኢ ምቦክ* የተባለውን የትውፊታዊ ተውኔት ቡድንም ለማቋቋም ችላለች፡፡ በመቶዎች ለሚቆጠሩ አስቸጋሪ የህይወት ፈተና ውስጥ ለገቡ ወጣቶች ልዩ ስልጠና በመስጠትም መልሳ ወደ ማህበረሰቡ በመቀላቀሏ *የ2000 ፕሪንስ ክለዐስ ሽልማት የ'ሂሮ ኦፍ ዘሲቲ'* ክብርን ተቀዳጅታለች፡፡ ከ2001 ጀምሮ የወጣቶችን የፈጠራ ስራ የሚያበረታታውን *ፓንአፍሪካን ካይአኢ ፋውንዴሽን* በማቋቋም የዜጎችን ህይወት እየለወጠች ትገኛለች፡፡

ዘርፈ ብዙ ክህሎቷ በርካታ ሽልማቶችን አስገኝቶላታል፡፡ *የአርሌቲ ፕራይዝ ከፈረንሳይ፣ የሬኔ ፕሬይል ሽልማት* ከቤልጂየም *፣ የፎንለን ኒኮልስ ሽልማት ከካናዳው አልበርታ ዩኒቨርሲቲ፣ ሽቫሊየ ዴ አርትስ ኤ ሌትህ ፍሮንሴይዝ፣ የኮትዲቯር ናሽናል ኦርደር ኦፍ ሜሪት ኮማንደር፣ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከፍተኛ ምክር ቤት አባል(1997 - 2003)፣ የኖማ ሽልማት(2005) እና የ2007 ዓመት የአመቱ ምርጥ መጽሐፍ የሎሬት ክብርን ዘ ሚሞሪ አምፒዩቲ በተሰኘው ረጅም ልብወለዷ ተቀዳጅታለች፡፡* በአሁኑ ወቅት በአይቮሪኮስት የሚገኘው የአፍሪካ እና የአፍሪካ ዳያስፖራዎች የሳይንስ፣ የጥበብ እና የባህል አካዳሚ ቋሚ አባል ነች፡፡

**ተርጓሚ - ምንያህል ተሾመ ቸሩ/** Translation : Menyahel Teshome Cheru

**የቴአትር መምህር፣ ጸሐፊና ተዋናይ/** Lecturer, Theater Practitioner

**ኢትዮጵያ/** Ethiopia